# <u>የኢትዮጵያ ፖለቲካ እያደር ይፋጃል???</u>

<u>**በነሲቡ ስብሐት**</u> USA. Virginia (nhsibhat@gmail.com) ግንቦት 27 ቀን 2015 ዓ.ም.

የሀገሬን ፖለቲካ ተካፍዬበትም ሆነ ዳር ተመልካች በመሆን ግማሽ ምዕተ ዓመት ለሚሆን አይቼዋለሁ ብል አልሳሳትም። ዴያስፖራ እየተባለ የሚጠራውንም አካል በትንሹ ለአለፉት 20 ዓመታት ነበርኩበት። በእኔ አመለካከት ሕይወት እራሱን የቻለ ትምህርት ቤት ነውና ከተመከሮ ብዙ ተምሬሃለሁ። ዛሬ የዚህ ጽሁፌ ዓላማ አሁን የኢትዮጵያ ፖለቲካ ደረሰበት ከምለው አኳያ ቀጣይ ዕጣችን ምን ሊሆን እንደሚችል ያለኝን አመለካከት ለማቅረብ ነው። ከነገ ዛሬ የሚሻለውን እያስተናገደች የመጣችው ሀገራችን ነገዋ ደግሞ ምን ሊሆን ይቃጣዋል?

በተቀነባበረ መልክ "ያ ትውልድ" የምንለው የ60ዎቹ እንቅስቃሴ ከተኮላሸ በኋላ ኢትዮጵያችን ሊታመን በማይችል መልኩ አንድነቷ ተናግቷል። ከዜነቿ የሀገርና ብሔራዊ ፍቅር ተሻግሮ ዛሬ ዘረኝነት እና ክልላዊነት ሀገር እያፈረሰ፣ ሕዝብ እያረደ፣ ትውልድ እየመረዘ አለበት ዘመነ መርገምት ላይ ደርሰናል። አንድ ሀገር በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚውና ማህበራዊ ጉዳዮች ቀውስ ውስጥ ስትዘፈቅ ብሔረተኝነት ስሜት ያቆጠቁጣል። አቆጥቁጦም አያበቃም ያልታሰበ አምባገነን ሊያበቅል ይችላል። ዛሬ ሀገር ከደረሰችበት እጅግ አስከፊ ሁኔታ አሁን ያለው በዶክተር ዐብይ አሕመድ የሚመራው ዘረኛ አሮሙማ ይወገድልን እንጂ የፈለገ ይምጣ ባዩ በበረከተበት ፖለቲካ ያለውን ሁኔታና ሊከሰት የሚችለውን መጠቆም ጊዜው ካልሆነ ወይም በተግባር እስኪታይ "ሌላ አታውሩን" ለሚሉ የሚያስከትለው መሰደብና ነቀፌታ ቢሆንም ተቀብሎ "ጆሮ ያለው ይስማ" " ዓይን ያለው ያስተውል" ለማለት ደፍሬሃለሁ።

አንዳንዶች ሂደታቸው እንዳይነገራቸው ወይም እንዳይታወቅባቸው "እሱን አታንሱት፣ አሁን ስለአለፈው መተረክ ምን ያስፈልጋል?" በማለት ሆይ! ሆይ! የሚሉበት ላይ ብቻ እንድናጨበጭብላቸው ይፈልጋሉ። የቅርቡን 1997 ዓ.ም. የወለደውን የቅንጅት ዘመን ብንቃኝ በነበረው ትርምስና ያልጠራ አሰላለፍ የተገኘውን ድል ለወያኔ አስረክቦ ዛሬ ለደረስንበት መከራ መዳረጋችን በወቅቱ የነበሩ "አትናገሩን" ባይ ፖለቲከኞች ነበሩ። ቀጠለ ኢትዮጵያዊነትን ለማረጋገጫ 500 ዶላር የሚያወጣ የፊርማ ቲኬት ሲሸጥ "ኧረባካችሁ!" ብንል ተሳዳቢዎቹና አንቋሻሾቹ ያንን ሁሉ የዲያስፖራ ዶላር ዘርፈው፣ ካኪ ሱሪና ጉርድ ሸሚዝ በወታደር ጫማ ተጫምተው "አርበኛ" በሉን ሲሉ ከነበሩት አንዳንዶች ዛሬ ትግሉን እንዴት እንደሸጡት ብቻ ሳይሆን ከአለው መንግስት ጋር እየተሞዳሞዱ አማራን ሲያስጨፈጭፉ፣ ሕዝብን ሲዘርፉ ስንታዘብ ከዚህ ካልተማርንና "አሁንም ምን እየተደረገ ነው?" ብንል አግባብነት አለው እላለሁ። ሌሎች ደግሞ በየስቴቱ እየዞሩ ብር ሰብሳቢ አክቲቪስቶች እና ባለ ሚዲያዎች በርስ በርሳቸው ሹኩቻ ከሥልጣኑም ከፖለቲካውም ወደ ዳር ሊገፉ ሲንደረደሩ ሌላ ቀዳዳ ሊሸነቁሩ ሲፍጨረጨሩ እየታየ ነው።

በቅርቡ ዶር ዐቢይ ለሥልጣን ሲበቃ በስሜት በመገፋፋት ብቻ አርቆ ከማሰብና ልምድን ተንተርሶ ሁኔታውን ከማገናዘብ ይልቅ "ተደመሩ" እያሉ ሌሎችን አፍ ያስይዙ የነበሩ ቀላል አልነበሩም። ዶር ዐብይ ገና ሥልጣን ሲይዝና "እኔ አሻግራችኋለሁ" ሲል አይሆንም ይሉና ያልን በጣት የምንቆጠር በወቅቱ የምንለው መሰማት አይደለም አፍ ማዘጋት ነበር የተያዘው። በመደመር ዘመን "የሽግግር መንግሥት" አስፈላጊነትን ያነሱ "ጊዜው ያለፈበት" እየተባሉ አንገታቸውን ለጊዜው ቢደፉም ዛሬ ግን ከማንም በላይ ለመናገር የሞራል ብቃት ያላቸው አድርጌ እወስዳቸዋለሁ።

ከላይ በመጠኑም ቢሆን ያስቀመጥኳቸው ነጥቦች ወደ ኋላ ዞር ብለን ስንቃኝ ከቻልን እራሳችንን እንድንታዘብ ብዬ ነው። <u>**የዴያስፖራው ፖለቲካ እኔ እንደታዘብኩት ሆይ ሆይ የበዛበት የገንዘብና የዝና ፈላጊዎች መድረክ ነው እላለሁ።**</u> ብቻ ዋናው ጨዋታቸው ከፊት ወቅታዊና ለጥያቄ የማያመች አጀንዳ ያስቀምጡና "አትናገሩን፣ አድምጡን፣ አሁን የተለየ አደረጃጀት ነው" ይሉናል። ለዚህ ደግሞ ከዋናዎቹ አቀንቃኞች በበለጠ መልኩ የገደላ ገደል ማሚቶ የሆኑ አክቲቪስቶች፣ ሚድያዎች፣ ሶሻል ሚድያዎች በፍጥነት ይቀባበሉላቸዋል፣ ያራግቡላቸዋል። ስም እየቀያየሩ ሁሌም ጨዋታውን የሚጫወቱት በአብዛኛው የተለመዱት እነኛው ሰዎች መሆናቸው ደግሞ "አይ ድፍረት" ያሰኘኛል። አሁን አሁን ደግሞ ሌሎችን ፊት ቀዳሚ በማድረግ ጨዋታው ከበስተጀርባም ተጀምሯል።

ውድ ወገኖች:- የታሪክ ድግግሞሽ ያልተለያት ሀገራችን ነገን ሳስበው፣ ማነው ባለተራ? ስል ተአምር ካልመጣ በቀር ገና ብዙ ጉዞ ይጠብቃታል። ዛሬ ሀገራችን የደረሰባትን ከባድ አደጋ ምክንያት አድርገንና አንዳንድ ታዋቂዎችን ከፊት አስቀድመን "የሀገር አንድነት፤ አማራው ተጨፈጨፈ" በሚል ሽፋን "ሌላ አትጠይቁን የምንለውን ገንዘብ ብቻ አምጡ" የትም አያደርስም።

ስለ አማራ መጨፍጨፍ፣ ኢትዮጵያችን ከባድ አደጋ ላይ ስለመሆኗ፣ አረመኔው የዐብይ አገዛዝ መወገድ እንደሚገባው ከዘረኞቹ በቀር ማንም ይስማማበታል። ይህንን ግና ተገን አድርጎ የደፈጣ ውጊያ ሲደረግ መጠየቅና መመርመር ተገቢ ነው። ከ1997

ዓ.ም. ገደማ ስዬ አብርሃና ገብሩ አስራት “ከወያኔ ተጣላን” ብለው ወደ ዲያስፖራው ሲመጡ ከመቀመጫ በመነሳት ያጨበጨበላቸው ሁሉ ዛሬ የት እንዳሉ ቢነግረኝ መልካም ነው። ትላንት “እሱን አትናገሩት” እየተባለ በየመድረኩ ሲያላግጥብን የነበረው ብርሃኑ ነጋ ዛሬ የት ነው ያለው? ዛሬ ስላለፈ አይደለም የሞተን አካባ አምጥቶ ሲተቃቀፍና ለዛሬ ስልጣናቸው የልብ ልብ ሲሰጣቸው “ኸረ ያገር ያለህ! የሕዝብ ያለህ!” ሲባል ሰማሁ ያለ፣ እውነት ያለ ማን ነበር? እና እናማ የሚያልፍ ስድብና ጩኸት ተፈርቶ ሊመጣ የሚችለውን አካሄድ ደፍሮ መናገር የኅሊና እረፍት ይሰጣል፣ ጆሮ ያለው ይሰማልና ድምጼን አሰማለሁ።

የ60ዎቹን ትውልድ ቅርጥፍ አድርጎ የበላው ደርግ ሀገር ወዳድ አልነበረም ለማለት ይከብደኛል። አዎ ከፍተኛ ሀገራዊ ስሜት፣ ከፍተኛ የባንዲራ ፍቅር የነበረው አገዛዝ ነበር። ግና ደርግ የምለውን ሁሉ ተቀበሉኝ፣ ሌላ ሀሳብ ሰጪም ይሁን ተቃዋሚ አልይ ባይ ነበር። ለየት ላለ ሀሳብ አቅራቢ መፍትሄ አድርጎ የወሰደው መደምሰስ፣ ማውደም፣ እርምጃ መውሰድ መሰል ቃላቶች የታጀበ ግድያ ነበር። ደርግ የተቃወመውን ብቻ ሳይሆን ያጨበጨበለትንም አልማረም። ሥልጣኑን ወዳድ አንድ ፈላጭ ቆራጭ አምባገነን በማፍራቱ የራሱን ሰዎች ጭምር እምሽክ አድርጎ በልቷል። ገና ከጅምሩ ሌሎችን እንተዋቸውና ጀኔራል አማን ሚካሄል አንዶም፣ ሻለቃ ኪሮስ ዓለማየሁ፣ ሻምበል ሲሳይ ሀብቴን፣ ጄነራል ጌታቸው ናደው፣ ሻለቃ አጥናፉ አባተን በሰበብ አስባቡ የረሸነ አገዛዝ ነበር። የጭካኔው መጠን በመውደቂያው መጨረሻ ላይ እውን ለመናገር የሱማሌ ጦርነትን ለድል ያበቁትን ምርጥ ከፍተኛ የጦር ጀነራሎችና መኮንኖችን በማጣጣም ለወያኔ ሥልጣን መብቃት በር የከፈተና የፈረጠጠ አረመኔ መንግሥቱ ኃ/ማርያም ነበር።

ኢሕአፓስ ሊገድለውም ሞክሮበት ነበርና በአጠፋው “ለአንድ ታጋይ ሺህ አናርኪስት” ብሎ እንደፎከረው ትውልድ አጥፍቶ ሀገሪቷን ለዛሬ ስለማብቃቱ ብዙ ትንታኔ ሊጠይቅ ቢችልም ስንት ንፁሃን እንዳለቁ የሚዘነጋ አይደለም። የደርግ ኢሠፓ ሰዎች እስከነ ወንጀላቸው በየቦታው መኖር ብቻ ሳይሆን ዋና የፖለቲካው ተሳታፊዎች መሆናቸው መናገር እችላለሁ። የደርግ ኢሠፓ ልጆች አይደሉም የዛሬ ወጣቶች በጥቅሉ “ደርግ ይሻለናል፣ ሀገር ወዳድ ነበር” ከሚል አልፈው “መንጌ ና ና” እያሉ ሰልፍ እስከመውጣት ቢደርሱ አይፈረድባቸውም። ዶር ዐብይ ለሥልጣን እንደበቃ ሀገር ቤት ሄጄ የታዘብኩት ቢኖር በአብዛኛው ታክሲና ባጃጅ የሕዝብ ማመላለሻዎች ላይ ዓፄ ኃይለሥላሴ፣ መንግሥቱ ኃይለማርያምና ዶር ዐብይ አሕመድ ምስል ያልለጠፈ ለማየት ይከብድ ነበር። በዚህ ግርግር የፋሽስቱ መንግሥቱ ኃይለማርያምን ማንነት ለመቀየር የተካሄደ የደርግ ኢሠፓ ኃይሎች እንቅስቃሴ እንደነበር ለመረዳት ጊዜም አልወሰደብኝም። ምክንያቱም ሀገራችን ላይ የደረሰው ግፍና በደል እንዲሁም የመበታተን አደጋ ይህንን ቢያስመኝ አይፈረድም። በሌላም በኩል የነበረው የያ ትውልድና የኢሕአፓ ታሪክ ትላንትም ዛሬም ታሪኩን እንኳ ለማስረዳትም ሆነ ለማስቀመጥ ጊዜ ሚዛኑን አልደፋለትምና በተገኘው አጋጣሚ መቀጥቀጥ የተለመደ ሆኗል።

ይህ ደግሞ ዝም ብሎ የመጣ ሳይሆን በተገኘው አጋጣሚ ማንንም የደርግ ኢሠፓ ወገንና አወቁም አላወቁም ያ ትውልድ እና ኢሕአፓን በመጥላት ብቻ ገና ስሙ ሲነሳ ዘለው “የሱማሌ ጦርነት፣ ተኩስ የጀመረ ድርጅት፣ የብሔር ጥያቄን ለዚህ ያደረሰ” በሚል የማጥቂያ አጀንዳዎች ላይ ብቻ ማተኮሩን በተደጋጋሚ ተያይዘውታል። በአብዛኛው ይህን የሚደጋግሙት አስከፊው የጭካኔ አገዛዛቸው ጎልቶ እንዳይታይ፣ እንዳይነበብ ስለሚፈልጉና ዳግም በሀገር አንድነት ስም ለዳግም ሥልጣን ስለቋመጡ ነው።

በአለፈው ዓመት ኢሠፓ እንደ ፓርቲ በሀገር ውስጥ እንዲመዘገብ ጥያቄ አቅርቦ በምርጫ ቦርድ መሠረዙ ይታወሳል። የኢሠፓ ያላቋረጠ እንቅስቃሴ በትንሹ በፈረንጆቹ አቆጣጠር 2013 በዲሲ በተካሄደው የሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያውያኖች ዓመታዊ ዝግጅት ወቅት በተጀመረ ስብሰብ ነው ማንሰራራት የጀመረው። ጊዜውንና ወቅቱን ሲያዩት የአንድነት ኃይል የሚባለውም ሆነ በኢሕአፓው በኩል ይንቀሳቀስ የነበረው የተዳከመና ሊስማማ የማይችል የትም የማይደርስ ኃይል መሆኑን በመገመት በሀገር ወዳድነት የማይታሙባቸው ሀገራዊ አጀንዳ በማንሳት እራሳቸውን አጉልተው ሊያወጡ የሚችሉበትን አቅጣጫ በመቀየስ መንቀሳቀስ በመጀመር ዛሬ ከሞላ ጎደል ከበስተጀርባ ዋናው የትግሉ አንቀሳቃሽ ሞተር ሁነዋል።

ቀደም ሲል ለምሳሌ በቅንጅት ዘመንና ከዚያ ወዲህ እቅዳቸው በሚፈጠሩ ማንኛውም የፖለቲካ፣ የሲቪክ ድርጅቶች ውስጥ በመሰግሰግ ለሥልጣን በሚበቃው ድርጅት አማካኝነት በቀጣዩ መንግሥት ወደ ተጠያቂነት እንዳይገቡና ታሪካቸውን ጥሩ ጎን በማጉላት ለመውጣት ነበር። ሆኖም ግና እያደር የሀገሪቷን ሁኔታ እና የሌላውንም መዳከም ሲያዩት አሁንም ወደ ሥልጣን መምጣት የማይችሉበት ምንም ምክንያት የለምና እንቅስቃሴአቸውን በሰፊው ከተያያዙት ከረምረም ብለዋል። ለዚህ ደግሞ በተለይ በዲያስፖራው ዘንድ ያሉትን አብዛኛውን ሚድያዎች፣ ድረ ገጽ በገንዘብ አቅም ጭምር ድጋፍ በመስጠት ተባባሪ ማድረግ ችለዋል። ይህ ደግሞ ከላይ እንደገለጽኩት የደርግ ዘመን ትውልዶች ዛሬ በ40 ውስጥ ያሉት “ደርግ ይሻል ነበር” ባዮች በርካቶች ናቸውና ተባባሪ ቢሆኑላቸው አያስደንቅም።

እንኳን የደርግ ዘመን ትውልድ አይደለም የያ ትውልድ ዘመን ሁነው ደርግ ያደረገውን አረመኔያዊ ድርጊት የሚረዱ እንኳን ያን ትውልድ በአገኙት መድረክ ሲያጠቁ ይስተዋላሉ። የፊታቸው ገጽታ እንዳላመኑበት እያሳወቀ፣ ጋዜጣዊ ሙያቸውን የሸጡ

የደርግ ኢሠፓ ልጆችን ሳያምኑበት ኢንተርቪው አድርገው የተርበተበቱም የቅርብ ትዝታዬ ነው። ይህ እና መሰል ኩነቶች ታዲያ ደርግ ኢሠፓ ለዳግም ሥልጣን የሚያደርገው ግስጋሴ የዛሬ እንዳልነበር ለመጠቆም ነው።

ታዲያ ይህ ሁሉ ትንታኔ ምን አመጣው? ትሉ ይሆናል። ዛሬ ሀገር በተተራመሰችበት ወቅት እልውናዋ አስጊ ሆኖ ሁሉም ወደ አምላኩ እየተማጸነ ባለበት ጊዜ" ምንስ ቢመጣ" ሊባል አይገባውም ባይ ነኝ። ድርግ ኢሠፓ በምንም መልኩ ለዳግም ሥልጣን መብቃት አይኖርበትም ባይ ነኝ። ለሥልጣን አለመብቃትና አብሮ መሥራት፣ በብሔራዊ ዕርቅ አብሮ መጓዝና ይቅር መባባል አግባብ መሆኑን አምንበታለሁ። ግና የደርግ ኢሠፓ ወንጀለኞች ዳግም ወደ ሥልጣን ኮርቻ በደርግና ኢሠፓ ስም ለመምጣት የሞራል ብቃትም ሊኖራቸው አይገባም ስል መጪውን መንግሥት ለመጠቆም እፈልጋለሁ።

እጅግ የመንግሥት አመሠራረት ልምድ ያላቸው የደርግ ኢሠፓ ስብስብ በአሁኑ ወቅት ከአለው መንግሥት ሳይቀር ተሰግስገው ሥራቸውን እየሰሩ ይገኛሉ። በሀገር ቤት በተለያዩ መንግሥታዊ መዋቅር ውስጥ ከመኖራቸው ባሻገር በየፖለቲካው ድርጅቶች ውስጥ ዋና ተሳታፊ በመሆን እንዴት አድርገው መጪውን ጊዜ የነሱ እንደሚያደርጉ እጅጉን ተግተውበታል። ለዚህ ደግሞ ቀዳሚውና ዋናው ተግባራቸው የሚከተሉት ናቸው፦

- በአገኙት አጋጣሚ ያ ትውልድን እና በተለይ ኢሕአፓን ስም ማጠልሸት፣
- በአሁኑ ወቅት አደባባይ ወጥተው ማንነታቸውን እና እንቅስቃሴአቸው ሳይታወቅባቸው መንቀሳቀስ
- ዋናዎቹ የደርግ ኢሠፓ ሰዎች ዕድሜአቸውም ስለገፋ ልጆቻቸውንና ደጋፊዎቻቸውን ከፊት ማስቀደም፣
- ደርግን ከፍ ሊያደርጉ በሚችሉ እይታዎች ለምሳሌ የሶማሌን ጦርነት አስታኮ የካራ ማራ ቀን ተብሎ ብሔራዊ በዓል ይሆን ዘንድ መግፋት፣
- ታዋቂ ያላቸውን የእቅስቃሴው አካላት አውቀውትም ሆነ ሳያውቁት በነሱ መዳፍ ውስጥ ማስገባት፣
- ወቅቱ የአማራው መጨፍጨፍ ስለሆነ ይህንን ሽፋን በማድረግ መንቀሳቀስ
- በውጭ የሚገኘውን የዲያስፖራ እንቅስቃሴ በደመዳፋቸው ማስገባት
- በውጭ የሚንቀሳቀሱ የሚዲያ ወገኖችን በመጠቀም የነሱን በጎ ጎን እንዲያጎሉ በተጨማሪ ማንኛውንም ደርግን የሚቃወም ኢንተርቪውም ሆነ ውይይት እንዳያቀርቡ በተለያየ መልኩ መቆጣጠር
- በውጭ የሚገኙ ድረ ገጾች ስለ ደርግ የሚቀርቡ አሉታዊ ትችቶችን እንዳያስተናግዱ መግፋት፣
- ከዚህ በፊት ደርግ ኢሠፓን የሚያጋልጡ ጽሁፎች፣ መግለጫዎች ከማንኛውም ሶሻል ሚድያ እንዲነሱና ደብዛቸው እንዲጠፋ ማድረግ፣

ወዘተ መሰል ክንዋኔዎች በሠፊው ዘመቻ ተያይዘውታል።

የዚህ ጽሁፌ መልዕክቱ አሁን ግልጽ የሆነ ይመስለኛል።

“ደርግስ ቢሆን ምን አለበት?” ለምትሉ ዛሬ ዘረኝነት በሰፈነበት አስከፊ አደጋ ላይ እያለን ዲያብሎስ ይሁን ሳትናኤል ብለን ማማረጥ አንችልምና ይሁንና ዳግም ከተቃዋሚነት አያውጣን ከማለት ሌላ የምለው የለኝም።

“የጉድ ሀገር ገንፎ ...” እንደሚባለው “የሀገራችን ፖለቲካ እያደር ይፋጃል” ልበለውና ቀጣይዋ ጠቅላይ ሚንስትር ዶር ትግሥት ሆና ለማየት ያብቃችሁ እያልኩ ልሰናበታችሁ።

የምችለውን ጠቁሜአለሁ ዛሬ ሳይሆን ወደፊት ታነቡት ይሆናል።

ፈጣሪ ኢትዮጵያን ይጠብቃት!!!

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!

የያ ትውልድ ታሪክ ህያው ነው!!!

ቸር ይግጠመን

ነሲቡ ስብሐት

ግንቦት 27 ቀን 2015 ዓ.ም. (June 3, 2023)